# የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
# የሰላምና አንድነት ጉባኤ

**Council of Peace and Unity of the Ethiopian Orthodox Tewahedo Church**

"የተረፈውንም ነገር ሳልቆጥር ዕለት ዕለት የሚከብደብኝ የአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ አሳብ ነው" (፪ ቆሮ ፲፩፥፳፰)

እሑድ፣ ኅዳር 30 ቀን 2005 ዓ.ም

**የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰላምና አንድነት ጉባኤ ከኅዳር 26-30 ቀን 2005 ዓ.ም (December 5-9, 2012) በዳላስ፣ ቴክሳስ ለሦስተኛ ጊዜ ባዘጋጀው ጉባኤ አበው ላይ ከኢትዮጵያና ከሰሜን አሜሪካ በቅዱስ ሲኖዶስ ተሰይመን በተላክን የሰላም ልኡካን የተሰጠ የጋራ መግለጫ።**

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን!

*"አንድ እረኛ፥ ለአንድ መንጋ" (ዮሐ. 10፥16)*

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የተፈጠረውን መለያየት አስወግዶ ሰላምንና አንድነትን ለማምጣት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰላምና አንድነት ጉባኤ ባደረገው ከፍተኛ ጥረትና በሁለቱም ወገን በተገኘው ፈቃድና ስምምነት መሠረት እነሆ በአሁኑ ጊዜ በሰሜን አሜሪካ ቴክሳስ ግዛት ውስጥ በሚገኘው ዳላስ ከተማ ከኅዳር 26-30 ቀን 2005 ዓ.ም በክራውን ፕላዛ (Crowne Plaza -14315 Midway Rd-Addison, Texas 75001) የሦስተኛው ዙር ጉባኤ ሊካሔድ ችሏል።

የጉባኤው ዓላማ መለያየት ተወግዶ ሰላምና አንድነት እንዲመጣ ማድረግ በመሆኑ ለዚሁ ዓላማ ስማችን ከዚህ በታች የተጠቀሰው ልኡካን በሰላምና አንድነት ጉባኤው ላይ በልኡክነት ተገኝተናል።

| ከኢትዮጵያ | ከሰሜን አሜሪካ |
|---|---|
| 1ኛ/ ብፁዕ ዶ/ር አቡነ ገሪማ ሊቀ ጳጳስ | 1ኛ/ ብፁዕ አቡነ መልከ ጼዴቅ ሊቀ ጳጳስ |
| 2ኛ/ ብፁዕ አቡነ አትናቴዎስ ሊቀ ጳጳስ | 2ኛ/ ብፁዕ አቡነ ኤልያስ ሊቀ ጳጳስ |
| 3ኛ/ ብፁዕ አቡነ ቀውስጦስ ሊቀ ጳጳስ | 3ኛ/ ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ሊቀ ጳጳስ |
| 4ኛ/ ንቡረ እድ ኤልያስ አብርሃ | 4ኛ/ ሊቀ ካህናት ምሳሌ እንግዳ |



EOTC Peace and Unity
P. O. BOX 505, Stone Mountain, GA 30086 E-mail: copauoeotc@yahoo.com

የሰላምና አንድነት ጉባኤው የቀረጸውን የጋራ አጀንዳ አይተን ካጸደቅን በኋላ የዕርቀ ሰላሙ ውይይት ጉባኤው ባወጣው መርሐ ግብር መሠረት ተካሔዷል። እንደሚታወቀው የዚህ ጉባኤ ውጤት የሠመረ እንዲሆን ሁላችንም ከልብ የምንፈልገው፣ መላው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ካህናት፣ ምእመናንና የሰንበት ትምህርት ቤት ወጣቶች በከፍተኛ ተስፋ የሚጠብቁት በመሆኑ ሁላችንም ለሰላሙ ሥምረት የሚጠበቅብንን ጥረት በቅንነትና በመግባባት ስናካሒድ ሰንብተናል።

ጉባኤው በመንፈስ ቅዱስ የተመራ በመሆኑ በአንደኛውና በሁለተኛው ጉባኤያት ከነበረው የበለጠ መግባባትና መቀራረብ የሰፈነበት፣ ሙሉ የሰላም ፍላጎት የታየበት ጉባኤ ነበር። ለዚሁም እንዲህ ያለውን መግባባት የተመላበት ጉባኤ እንድናካሒድ ላደረገ እግዚአብሔር ክብርና ምስጋና ይድረሰው እንላለን። በዚህ ጉባኤ ከተነሡት ዐበይት ጉዳዮች መካከልም ዋናውና ወሳኙ አጀንዳ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ወደ ቅድስት አገራቸው ኢትዮጵያ ስለሚመለሱበት ጉዳይ ነው። በዚሁም ቅዱስነታቸው ወደ አገራቸው ይመለሱ የሚለው መሠረታዊ ሐሳብ በሁላችንም በኩል ተቀባይነትንና ስምምነትን አግኝቷል። በዚሁ ጉዳይ ላይ ያልተስማማንበት ነጥብ ቢኖር ቅዱስነታቸው እንዴት ወይም በምን ሁኔታ ይመለሱ በሚለው ነጥብ ላይ ነው።

ይኸውም ልዩነቱ ከኢትዮጵያ ልኡካን በኩል የቀረበው አቋም ቅዱስነታቸው መሠረታዊ ፍላጎታቸው ተሟልቶላቸው፣ ክብራቸውና ደረጃቸው ተጠብቆ በመረጡት ቦታ ይኑሩ የሚል ሲሆን፤ በአንጻሩ ደግሞ ከሰሜን አሜሪካ ልኡካን በኩል ቅዱስነታቸው ከነሙሉ ሥልጣናቸው ወደ መንበራቸው ሊመለሱ ይገባል የሚል አቋም ነው። ይሁን እንጂ በውይይቱ ጊዜ አንዱ የሌላውን መብት ጠብቆ በመከባበር ውይይቱ በሰላምና በመግባባት ተካሒዷል። በመሆኑም ከሰፊ ውይይት በኋላ የሚከተለውን የጋራ መግለጫ አውጥተናል።

## <u>የጋራ መግለጫ</u>

1ኛ/ እንደሚታወቀው የሰላምና አንድነት መሪና አስተማሪ ሆና ለዘመናት ሕዝቧን ስትመራ የኖረችው ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን በዘመናችን ሰላምንና አንድነትን ማጣቷ መላውን የቤተ ክርስቲያን ልጆች በእጅጉ እያሳዘነና እያሳሰበ ያለ ዐቢይ ጉዳይ ነው። በመሆኑም በአሁኑ ለሦስተኛ ጊዜ የተደረገው የሰላም ጥረት ከመጨረሻ ፍጻሜ ላይ መድረስ ባይችልም የሰላሙ አጀንዳ ከማንኛውም ጉዳይ ቅድሚያ ሊሰጠው ስለሚገባ ቀጣዩና አራተኛው ዙር የሰላምና አንድነት ጉባኤ ለሠመረ ውጤት እንዲደርስ በሁላችንም በኩል ያላሠለሰ ጥረት እንዲደረግ፤


EOTC Peace and Unity
P. O. BOX 505, Stone Mountain, GA 30086 E-mail: copauoeotc@yahoo.com

2ኛ/ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ወደ ቅድስት አገራቸው ኢትዮጵያ ስለሚመለሱበት ሁኔታ ከሁለታችንም የተሰጡ ምክንያቶች በሚገባ በዝርዝር ታይተውና ተጠንተው በሁለታችንም ወገን ምልዓተ ጉባኤ እየተመከረባቸው የመጨረሻ ውሳኔ እንዲያገኙ እንዲደረግ፤

3ኛ/ የቤተ ክርስቲያኑን ሰላምና አንድነት ለሚናፍቀውና ውጤቱንም በተስፋ ለሚጠባበቀው ሕዝባችን የሰላሙንና አንድነቱን ውጤት የማብሠሩ ጊዜ እንዲፋጠን ሁሉም በጸሎትና በሚያስፈልገው ሁሉ ለዚህ የተቀደሰ ዓላማ ድጋፉንና ትብብሩን እንዲያደርግ አደራ እንላለን፤

4ኛ/ የሰላሙ ጥረት ለፍጻሜ እስከሚደርስ ድረስ በሁለታችንም በኩል ለሰላሙ መሰናክል የሚሆኑ ማናቸውንም ሥራዎች ከመሥራት ተቆጥበን በትዕግሥት መጠበቅ ይኖርብናል፤

5ኛ/ ይህን መሠረታዊና ታላቅ የቤተ ክርስቲያናችንን ጉዳይ ለማሳካት ያላሰለሰ ጥረት በማድረግ ላይ ያለውን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰላምና አንድነት ጉባኤን ከልብ እናመሰግናለን፤

6ኛ/ የሰላምና አንድነት ጉባኤው ባቀረበው ሐሳብ መሠረት ቀጣዩና ፀራተኛው የዕርቀ ሰላም ጉባኤ ከጥር 16-18 ቀን 2005 ዓ.ም (January 24-26, 2013) በሎስ አንጀለስ፤ ካሊፎርኒያ እንዲካሔድ ተስማምተናል። ለዕርቀ ሰላሙ ስኬታማነት በሰላምና አንድነት ጉባኤው የሚሰየሙ ልኡካን ወደ ሁለታችንም ምልዓተ ጉባኤ በቅርቡ ተልከው ተገቢውን የማግባባትና የማቀራረብ ሥራ እንዲሠሩ እንዲደረግና እኛም ለሰላምና አንድነት ጉባኤው ልኡካን አስፈላጊውን ትብብር ለማድረግ ተስማምተናል።

7ኛ/ ይህ ጉባኤ ተጀምሮ እስከሚፈጸም ድረስ በዳላስ ደብረ ምሕረት ቅዱስ ሚካኤል ካቴድራል አስተባባሪነት በጸሎታቸው፣ በገንዘባቸው፣ በጊዜያቸው፣ በዕውቀታቸውና በጉልበታቸው ሰፊ አገልግሎት ያበረከቱትን የዳላስና አካባቢው ማኅበረ ካህናትንና ምእመናንን እንዲሁም የሰንበት ትምህርት ቤቶች ወጣቶችን ሁሉ ከልብ እናመሰግናለን፤ ስላደረጉልን መልካም አቀባበልና ከፍተኛ መስተንግዶ ሁሉ እግዚአብሔር አምላክ እንዲባርካቸውና በቸርነቱም እንዲጠብቃቸው እንጸልያለን።

በመጨረሻም የሦስተኛው ዙር የዕርቀ ሰላም ውይይት ውጤት ተስፋ ሰጪ በመሆኑ በአንዳንድ መገናኛ ብዙኃን በሚተላለፉ የተሳሳቱ መረጃዎች አማካይነት ሕዝበ ክርስቲያኑ እንዳይደናገር አደራ እንላለን።

እነሣሥኦ ላስጀመረን፤ አስጀምሮም ላሰፈጸመን ለልዑል እግዚአብሔር ክብርና ምስጋና ይግባው።



EOTC Peace and Unity
P. O. BOX 505, Stone Mountain, GA 30086 E-mail: copauoeotc@yahoo.com

## ከኢትዮጵያ

1ኛ/ ብፁዕ ዶ/ር አቡነ ገሪማ ሊቀ ጳጳስ ________

2ኛ/ ብፁዕ አቡነ አትናቴዎስ ሊቀ ጳጳስ ________

3ኛ/ ብፁዕ አቡነ ቀውስጦስ ሊቀ ጳጳስ ________

4ኛ/ ንቡረ እድ ኤልያስ አብርሃ ________

## ከሰሜን አሜሪካ

1ኛ/ ብፁዕ አቡነ መልከ ጼዴቅ ሊቀ ጳጳስ ________

2ኛ/ ብፁዕ አቡነ ኤልያስ ሊቀ ጳጳስ ________

3ኛ/ ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ሊቀ ጳጳስ ________

4ኛ/ ሊቀ ካህናት ምሳሌ እንግዳ ________



EOTC Peace and Unity
P. O. BOX 505, Stone Mountain, GA 30086 E-mail: copauoeotc@yahoo.com